# መልካም ዘመን

**የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ጥንት ከሚለው ቃል ይጀምራል፡፡** ጥንት የሚለው ቃል መገኛን መጀመሪያን ጀማሪንና አስጀማሪን ያመለክታል:: ለሀልዎቱ ጥንት የሌለው አምላክ እግዚአብሔር ዘመናትንና የዘመናትን መሥፈሪያ የሰጠን የዘመናት ባለቤት ነው፡፡ በባሕርዩም ፍጹም፣ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው አምላክ ነው፡፡ ፍጥረት በመፍጠሩ ሥራውን የገለጠ በመሆኑ የተረዳ ሆኗል፡፡ ይኸውም እርሱ በወደደ በፈቀደ መጠን ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ፍጥረትን በመፍጠር /በሥራው/ ሲገልጥ ለፈጠረው ፍጥረት መለኪያ መወሰኛ ጊዜንም አብሮ ፈጥሮአል፡፡ ጊዜውንም በሰባት ዐበይት ምሕዋራት /መመላለሻዎች/ ከፍሎታል፡፡ እነዚህም ሰባቱ ዕለታት ናቸው፡፡

ዕለታት በብርሃንና በጨለማ ዑደት /መፈራረቅ/ እንዲታወቁ “ጠዋትም ሆነ ማታም ሆነ አንድ ቀን” በማለት የሥነ ፍጥረት ሥራዎቹን ያከናወነበትን አንድ ሳምንት በመቁጠር አመልክቷል፡፡ /ዘፍ.1÷1/ ብርሃንና ጨለማ ተፈራርቀው ዕለታትን በሰባቱ ምሕዋራት እየተመላለሱ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ረዥም ዘመናት ተቆጠሩ፡፡ እግዚአብሔር የዘመን ቁጥርን በሥራው እንዳሳወቀን፤ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠርም ዘመናትን በድርጊት ከፍሎ የታሪክ ዘመኑን በሁለት ጎራዎች ዘመነ ብሉይ ዘመነ ሐዲስ ወይም ዓመተ ዓለም እና ዓመተ ምህረት እያለ ይቆጥራል፡፡

**ዘመነ ብሉይ /5500 ዓ.ዓ/** ለመላው የሰው ልጅ መልካም የሚባል ጊዜ አልነበረም፡፡ በዲያብሎስ እስራት እየማቀቀ የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን እየተጠባበቀና እየናፈቀ የኖረበት ዘመን ነበርና፡፡ ስም አጠራሩም ዘመነ ፍዳ፣ ዓመተ ኩነኔ . . . የሚባል ነበር፡፡

ርግበ ኖኅ የጥፋት ውኃ መጉደሉን የጥፋት ጊዜ ማለፉን ታበስር ዘንድ ለምለም ቅጠል ይዛ እንደተመለሰች፡በቀዳማይ ሺህ ዓመት መግቢያ ላይ በነቢይ “ቃለ ዐዋዲ” ተብሎ የተነገረለት መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የአዲስ ዘመን ዜና ብሥራትን ነገረን፡፡ “የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ..” በማለት የመጻኢውን ዘመን ብሩህነት፣ መልካምነትና የለውጥ ዘመንነት ለማየት ለሚወድዱ ሁሉ በንስሐ ጥምቀት እንዲዘጋጁ ሰበከ፡፡ /ማር.1÷2/

ከመጥምቁ ዮሐንስ ቀጥለው የዚህን ዘመን /የዘመነ ሐዲስን/ ዜና ብሥራት ለሰው ልጆች የነገሩ የሰማይ መላእክት ነበሩ፡፡ “ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት .. ተወልዶላችኋል” የሚለው የመላእክት የደስታ መግለጫ ቃል “ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ” በሚለው ዝማሬ መላእክት የታጀበ ነበር” /ሉቃ.2፥14/:: ክርስቲያኖች ከመላእክተ እግዚአብሔር በተማርነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊት /ውርስ/ አማካኝነት፤ ለሰው ወገን ሁሉ የመልካም ምኞት መግለጫችንን በልዩ ልዩ መንገድ “መልካም ዘመን” እያልን እንገልጻለን፡፡ ቃሉ የታወቀና ሕፃናትና አዋቂዎች፣ ግለሰቦችና ድርጅቶች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የእምነት አባቶች እና ሌሎችም በዘመን መለወጫ በዓል የማይዘነጉት ነው፡፡

እድሜአችን ላይ ይህን አዲስ ዓመት በየጨመረልን እግዚአብሔር በቅዱስ መጽሐፉ አማካኝነት “መልካም ዘመን” ይለናል፡፡ አዲስ ዘመን የሰጠን የዘመናት ባለቤት ፈቃዱን ፈጽመን የርስቱ ወራሾች የምንሆንበትን የንስሐ ዘመን

ጨምሮልናል ፤ እንደ ሸማኔ መወርወሪያ በሚፈጥንና በሚያልፍ ጊዜ ውስጥ ወደማያልፍ ክብርና ዓለም የሚያሻግረንን ሥራ የምንሠራበትን "ዓመተ ምህረት" አቀናጅቶናል፡፡ /መዝ.64÷11/

የበዓላት ሁሉ ራስ የሆነውን የዘመን መለወጫ በዓል ስናከብር ስለምንሰጣቸውና ስለምንቀበላቸው ስጦታዎች ወይም ስለ በዓሉ ድግስ አስቀድመን እናዘጋጃለን፡፡ በውኑ ይህ ዘመናችንን መልካም ሊያደርገው ይቻለዋልን?

ወዳጆቻችን "መልካም ዘመን" ሲሉንና እኛም አጸፋውን ስንመልስ "መልካም ዘመን" ማለታችን ምን ማለታችን ነው? ዘመንን መልካም የሚያደርጉትስ ምንድን ናቸው?

## 1. ዘመኑን መዋጀት /ኤፌ.5÷11/ ፡-

**ዘመንን መዋጀት የዘመንን ሁኔታ መረዳት ነው፡፡** "እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ፡፡" /ኤፌ.5÷11/ የሚለው መልእክት ያስተላለፈልን ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው ጥበበ ሃይማኖትን የያዘ ምእመን በሃይማኖት ሚዛን ዘመኑን ይዋጃል፡፡

የሰው ልጅ የፀሐይና የዝናብ ወራትን ለይቶ አውቆ የሚለብሰውንና የሚመገበውን ፣የሚወጣበትንና የሚገባበትን ለይቶ የሚያደርግ ከሆነ? በቀንና በሌሊት እንዴት አድርጎ መንፈሳዊ ሰውነቱን ይጠብቅ ዘንድ እንዳለው አያውቅምን? ቅዱስ መጽሐፍ "በለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል" ይላልና /ምሳ.18/:: ገበሬ ዘመኑን ዋጅቶ በሚዘራበት ወቅት የሚዘራ፣ የሚያርምበትም ጊዜ የሚያርም፣ አጸዱን የሚጠብቅ ከሆነ በመሰብሰብ ዘመን ደግሞ የሚሰበስብ ከሆነ ፍሬውን እንዳይበላ የሚከለክለው ማነው? ወይን ቦታ የተባለ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን እየተንከባከብን የወይኑ ባለቤት ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ፍሬ አልባ ሆነን እንዳንገኝ የተሰጠን ዘመን ፍሬ የምናፈራበት ዘመን መሆኑን እንረዳ፡፡ ዘመኑን መዋጀት ያስፈልገናል::

**"መልካም ዘመን" የሚሉን ወዳጆቻችን ሁሉ በሌላ መልኩ ዘመኑን ዋጁ እያሉን ነው፡፡** ዘመንን መዋጀት ማለት ምን ማለት ነው? ያለፈው ዘመናችንን ሂሳብ ዘግተን በተሰጠንና በቀረልን አዲስ ዘመን መልካም ለመሥራት መዘጋጀት ነው:: የንስሐን ጥምቀት ለኃጢአት ሥርየት እያጠመቀ የመጣው መጥምቁ ዮሐንስ ዘመኑን በአግባቡ የተረዳ ነቢይ ነበር፡፡ ምእመናንን እንዴትና በምን ሁኔታ ውስጥ ማዘጋጀት እንደነበረበት የሚያውቅ ፣ መቼ ማስተማር መቼ ማጥመቅ እስከ መቼ መሰብሰብና ወደ ማን መላክ እንዳለበት የተረዳ ነበር፡፡ ዘመኑን የዋጀ ነበርና ዘመን የሚገድባቸውን ምድራውያን ነገሥታትና የላከውን አምላክ በሚገባ ለይቶ በንጉሡ ማባበያ አልተታለለም፤በንግሥቲቱም ማስፈራሪያ አልደነገጠም::

**ነቢዩን ዘመኑን እንዲዋጅ የረዱት ነገሮች ምንድ ናቸው?** የመጀመሪያው የተጠራበትን ዓላማና የተሰጠውን ድርሻ መለየቱ ነው፡፡ ለዚህም በምድረ በዳ ብቻውን በመቆየት በቂ ዝግጅት አድርጓል:: አይሁድ የሚወዱትን ኤልያስን ነህን? ቢሉትም አይደለሁም አለ:: በተስፋ የሚጠብቁትን መሲሁ ነህን? አሉት:: እርሱም በትህትና ቃል መለሰላቸው "ከእርሱ የማንስ የእግሩንም ጫማ ልፈታ የማይገባኝ ነኝ" ሲል:: ዘመኑን የዋጀ ለሚያልፍ ክብር የማያልፈውን ፣ ለግዜያዊ ፍላጎቱ ዘላለማዊውን አይለውጥም:: የሥጋን መከራ እንኳን ተሰቆ ዘላለማዊ ሕይወቱን ገሀነም አይወረውርም:: ዘመኑን ዋጅቷልና በንስሐ በበጎ ምግባር ዘመኑን መልካም ያደርጋታል::

**ዮሐንስ ደቀመዛሙርቱን ፍጹም ክብር ወደሚያገኙበትና ወደ እውነተኛው መንገድ ልኳቸዋል፡፡** በእጁ የውኃን ጥምቀት የሚጠመቁ የበዙትን ምእመናንንም ማንነቱን የተረዳ ዘመኑን የዋጀ ይኸ መንፈሳዊ አባት "እኔ ዝቅ ዝቅ ልል ይገባኛል" በማለት በልጅነት ጥምቀት አክብሮ የመንግሥቱ ወራሾች ሊያደርጋቸው

ወደሚችል አምላክ አቅርቧቸዋል፡፡ መምህራንና ካህናት ዘመኑን መዋጀት ሲጀምሩ ወደ እነርሱ የሚሰበስቧቸውን ምእመናን በንስሐ አዘጋጅተው ለቅዱስ ቁርባን ያበቋቸዋል፤ ለበጎ ምግባር ያነቋቸዋል::

**ዘመኑን የዋጀ ምእመንም በሃይማኖት ብቻ እጸድቃለሁን ትቶ በየዘመኑ ምግባርና ትሩፋቱን እየጨመረ ይኖራል፡፡** የሚጠራበትን ጊዜ ወይም ነፍስ ከሥጋው መቼ እንደምትለይ ማወቅ ሰለማይችል ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሆኖ "የመዳን ቀን አሁን ነው" ይላል፡፡ ያለንበት ዘመን ነገሮች በፍጥነት የሚቀያየሩበት፣ ኢጋንንት የሠለጠኑበት፣ በወንጌል ስለ ምጽአት ዘመን የተነገሩ ትንቢታዊ ምልክቶች የሚታዩበት የፍጻሜ ዘመን መባቻ ላይ ነን፡፡ /ማቴ.24/ አንድ ምእመን ከዚህ ተነስቶ ነው ዘመኑን በመዋጀት ቅድስናን ገንዘቡ አድርጎ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝበትን ሥራ ለመሥራት መትጋት የሚጀምረው፡፡ እነሆ "መልካም ዘመን"

## 2. ዝግጅት ማድረግ /ዘጸ.12/ ፡-

ዘመኑን መዋጀት የቻለ ምእመን የዘመኑን ቁጥር ብቻ ሳይሆን ራሱን ለማዳንና ነጻ ለማውጣት ይዘጋጃል:: ምን ዓይነት ዝግጅት ማድረግ እንዳለበትም ያውቃል፡፡ አዲሱን ዓመት ለማክበር ብቻ አይደለም ለመቀበልስ ምን ዝግጅት አድርገናል? ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ሕይወት ዝግጅት ሲያስተምር ዘወትር የተዘጋጀን እንድንሆን ቢያስተምርም የንቃት ደወል የሚደወልባቸውና የንስሐ ጥሪ የሚያስተጋባባቸው ብዙ ዐውዶች አሉት:: ከነዚህ መካከል የዘመን መለወጥ የመጀመሪያው ነው:: ቅዱስ መጽሐፍ ስለ አዲሱ ዘመን ዝግጅት ምን ይላል?

የዚያን ዘመን የዘመን መለወጫ በዓል ከወትሮው ለየት ያለ ነበር፡፡ በዚያ ዓመት የተቀየረው የዘመኑ ቁጥር የወርና የዕለቱ ስያሜ ብቻ አልነበረም፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ታሪካቸውም ሕይወታቸውም የተለወጠበት መልካም ዘመን ነበር፡፡ ለዚህ የረዳቸው ደግሞ ዝግጅታቸው ነው፡፡ እርስዎ በአዲስ ዘመን ምን ለማድረግ ተዘጋጅተዋል? ከእስራኤል ዘሥጋ ዝግጅት ምን እንማራለን፡፡ /ዘጸ.12/ እስራኤል አዲሱን ዘመን መልካም ለማድረግ ሁለት ዓይነት ዝግጅት አድርገዋል ፡-

## ሀ. ከሞት ለመዳን ተዘጋጅተዋል:: /ዘጸ.12፥12/

የዘመን መለወጫ በዓልን ከፋሲካ በዓል ጋር የሚያከብሩት እስራኤል የበዓሉን ዝግጅት ቀደም ብለው ጀምረውታል፡፡ የግብጽ የገበያ ሥፍራዎች በገዢዎች ተጨናንቀዋል፣ በተለይ በበግ ሽያጭ ገበያው ጦፏል ሌሎቹም እንደዚያው፡፡ እስራኤል ይኽን ያደረጉ የነበረው ግን ለበዓሉ ድምቀት አልነበረም፡፡ የዚህ ሁሉ ዝግጅት ዓላማ አንድ ነው ከሞተ በኩር መዳን፡፡ /ዘጸ.12፥3/:: እግዚአብሔርም በግብጽ ሀገር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው "እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ አገር አልፋለሁ፥ በግብፅም አገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኵርን ሁሉ እገድላለሁ በግብፅም አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።" ከሚለው የእግዚአብሔር ፍርድ ለመዳን፡፡ /ዘጸ.12፥12/::

**አዲሱ ዓመት ድርብ በዓል የሆነላቸው እስራኤል በዓልን ለማድረግ ያደረጉት ዝግጅት የተመጠነና ለአንድ ዓይነት ዓላማ /ግብ/ የተዘጋጀ መሆኑ የሚያስተምረን ምንድን ነው?** የዘመን መለወጫ በዓል ድግስና ወጪያችን የተመጠነና ለአንድ ዓይነት ዓላማ የተዘጋጀ ነው? ለበዓሉ ድምቀት ስንጨነቅ ከበዓሉ መከበር ልናገኛቸው የሚገቡ በረከቶች እየተዘነጉ አይደለምን? አዲስ ዘመን መጻኢ ዕድልንና አዲስ ሕይወትን ለማየት የሚጓጓበት እንደመሆኑ ተፈጥሮ ሳትቀር በአደይ አበባ ለምልማ መልካም ዘመን

እያለች ልምላሌ ሕይወትን የምትሰብክበት ወቅት ነው፡፡ ታዲያ ሌላው ሁሉ ቀርቶ ከተፈጥሮ ተምሮ ቀጣዩን ዘመኑን መልካም ለማድረግ የተዘጋጀ ማን ነው?

**በዘፈንና በስካር በሌሎችም ኃጢአቶች የሚከበር የእግዚአብሔር በዓል የለም፡፡** የበዓላት ዓላማና አሳብ መንፈሳዊ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ በዓሉ መጪው ዘመን በሕይወት የመቆየትና ከሞት የመዳን ዓላማ ሊኖረው የተገባ ነው፡፡ እነዚህ ሕዝቦች የበዓሉን ድግስ ሲያዘጋጁ ሊበሉና ሊጠጡ በሥጋም ደስ ሊላቸው ብቻ አልነበረም፡፡ የመንፈሳዊ በዓል ዝግጅት ዓላማ በዓል ማድመቅ አይደለም፡፡

በዘመን መለወጫ በዓላችን የሚቀየረው የዘመኑ፣ ቁጥር የወራቱ ስም ብቻ ነው? አብረን ልንቀይራቸው የተዘጋጀነው ታሪክና ሕይወት የለምን? እስራኤል ዘሥጋ "ከሞተ በኩር" ለመዳን ከሞት ለማምለጥ ተዘጋጅተዋል፡፡ እኛስ? የክርስቲያኖች "ሞተ በኩር" ከሆነው ኃጢአት በንስሐ ለመዳን አንዘጋጅምን? ኃጢአት የምትወልደው ሞት ደጃፋችንን እንዳያንኳኳ አልፎ እንዲሔድ በንስሐ በቅዱስ ቁርባን እንዘጋጅ፡፡ ይኸ ነው ዘመንን መልካም የሕይወት ዘመን የሚያደርገው፡፡ መልካም ዘመን፡፡

## ለ. የነጻነት ጉዞ ለመጀመር ተዘጋጅተዋል፡፡

አዲስ ዘመን በአዲስ ጎዳና፣ በአዲስ አስተሳሰብ፣ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ርእይ ወዘተ የምንጓዝበት የአዲስ ሕይወት ምዕራፍ መጀመሪያ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስራኤል ዘሥጋ ለ430 ዘመን ያስቆጠረውን የባርነት ቤት የዘመን ሽግግር የማይቀረው የዘመን ዑደት ብቻ አድርገውት ኖረዋል፡፡ "ዓመት ዓመት ያድርሰን" እያልን የምንቆጥረው ዘመን ለዓመቱም እንዲሁ ሊያደርሰን ይችላል፡፡ ዓመት ዓመትን ወልዶ ልጅነት በወጣትነት፣ ወጣትነት በጉልምስና፣ ጉልምስና በአረጋዊነት ሲተካ በእኛ ሕይወት ምን ተለውጧል? የዘመን ዑደት ተፈጥሮአዊና እኛ ብንኖርም ባንኖርም የሚኖር ሒደት ነው፡፡

በጥንታውያን የመካከለኛው ምሥራቅ ነዋሪዎች ዘንድ የዘመን መለወጫ /አዲስ ዓመት/ የሚውልበትና በሥነ ፍጥረት ትምህርት መሠረት ሕይወት የሚጀመርበት ቀን የሚውለው በተመሳሳይ ጊዜ ነበር፡፡ እስራኤል ዘሥጋ ደግሞ "ኒሳን" እያሉ በሚጠሩት የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ወር ጋር የነጻነት በዓላቸውን ጨምረው ያከብራሉ፡፡ /ዘጸ.12፥14/ የምህረት ዓመትን ስንቆጥር አብረን ደግሞ የምንቆጥረው በጌታችን ያገኘነውን ነፃነትም ነው፡፡ ስለዚህ የዘመን መለወጫ በዓላችን የነፃነት በዓላችንም ነው፡፡ "በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።" /ገላ.5፥1/፡፡ ሰውነቱ ታሞ በከፋ ደዌ እየተሰቃየ ያለን ሰው ማን እንኳን ከዘመን ዘመን አሻገረኸ ይለዋል? ለሞት የሚያደርስ የጸና ሕማሙን በማሰብ ሁላችን እግዚአብሔር በሰላም እንዲያሰናብተው እንመኝለታለን እንጂ፡፡ ስንቶቻችን በኃጢአት ደዌ ተይዘን በከፋ የዲያብሎስ እስራት ውስጥ እየኖርን "እንኳን አደረሰህ/ሽ?" እየተባልን ነው? ለዚህም ሕይወት ከመጠን ያለፈና የበዛ የበዓል ዝግጅት እናደርጋለን፡፡ ለነፍስ ደግሞ ዝግጅት የምናደርገው መቼ ነው? ለነፃትስ?

**ዘመናችንን መልካም የሚያደርገው የድግስ ብዛት የበዓልም ድምቀት አይደለም፡፡** ለለውጥ መነሳታችን እንጂ፡፡ እስራኤል ዘሥጋ ታሪክንና ሕይወትን የቀየረ የዘመን መለወጫ በዓል ያከበሩት ለነፃነት በመዘጋጀት ነው፡፡ እንደ ሰው የግል ፈቃድ፣ እንደ ማኅበረሰብ የዜግነት ነፃነት ሳይኖራቸው ለግብጻውያን ጭቃ እያቦኩ ድንጋይ እየተሸከሙ ያለዋጋ የኖሩባቸው ዘመናት ረጅም ናቸው፡፡ በነዚህ ዘመናት ላባቸውን ብቻ ሳይሆን ደማቸውን፣ ጉልበታቸውን ብቻ ሳይሆን አጥንታቸውን ገብረዋል፡፡ ነፃነታቸውን ግን ማግኘት አልቻሉም፡፡ በአንድ ዘመን ግን አዲሱ ዓመት የሰላም የጤናና የብልጽግና እንዲሆን ተመኙ፡፡ ተመኝተው ብቻም አልቀሩም ካለፉት ዘመናት ይልቅ ካለፉትም በዓላት በተለየ

ሁኔታ ተዘጋጁ፡፡ ለነፃነት ጉዞ ከባርነት ቤት ማርና ወተት ወደ ምታፈስሰው ከነዓን አልዋሉም አላደሩም፡፡

"የመዳን ቀን አሁን ነው" ከሱስ ባርነት ከኃጢአት ባርነት፣.... ነፃ የምንወጣው መቼ ነው? በአዲሱ ዓመት የነፃነት ጉዞን የሚጀምር ማን ነው? እግዚአብሔር ካለበት የነፃነት ቤት ይልቅ በባርነት ቤት መቆየትን የሚመርጥ ሊኖር ችላልን? የሲኦል ደጆች ተከፍተው ከጨለማ ግዞት ነፍሳት እየወጡ ወደ ገነት ሲሔዱ እያየ በሲዖል መቆየትን የሚመርጥ ማን ነው? አሁን እግዚአብሔር የሚጠይቀን እንዲህ እንድናደርግ ነው፡፡

**"ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው ማን ነው? በጎ ዘመንን ለማየት የሚወድድ" ይለናል /መዝ.33÷12/፡፡**

መልካም ዘመንን ማየት የሚወድድ ሰው እንዴት በኃጢአት መቆየትን ሊመርጥ ይችላል? በቀጣዩ ዘመን መልካም እንዲደረግልን የነፃነት ጉዞ እንጀምር፡፡ በቀጣዩ ዓለም መልካም እንዲገጥመን ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው፣ ከሚጠፋው ወደ ማይጠፋው፣ ከዚህ ዓለም ገዥ ወደ ፈጣሬ ዓለማት የነፃነት ጉዞ እንጀምር፡፡ አዲስ ዓመት አዲስ የሚሆነው ወደ አዲስ ሕይወት በመምጣት የምናከብረው ሲሆን ነው፡፡ ለዚህ ነው እስራኤል አዲሱን ዓመት "ፋሲካ" ሽግግር በማለት የማያከብሩት፡፡ የክርስቲያናዊ ሕይወት ሽግግር እናድርግበት፡፡

መልካም ዘመን ሲሉን ስንልና ስንባባል ምን እያልን ምን እያሉንና ምን እየተባባልን እንደሆነ እናስተውል:: ከደቂቃ ቅንጣት እስከ ዘመናት ዕድሜ ታላቁን የጊዜ ስጦታ የሰጠን፣ ዘመናችንን ከዓመተ ፍዳ/ኩነኔ/ ወደ ምሕረት ዓመት የለወጠልን የዘመናት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ስጦታ በአግባቡ መጠቀም የሚጀምረውም ከደቂቃ ቅንጣት ነው፡፡ "በጥቂቱ የታመነ በብዙ ይሾማል" እንደተባለ ውሱን የሆነውን ምድራዊ ሕይወት በአግባቡ የሚያጠናቀቁ ሁሉ የደቂቃና ሰዓት፣ የዕለታትና ዓመታት ልኬት፤ የፀሐይና የጨረቃ ዑደት ወደሌለበት ዘለዓለማዊ ሕይወትን ከእግዚአብሔር ጋር ይኖሩ ዘንድ ይሾማቸዋልና ጊዜያችንን በአግባቡ እንጠቀምበት፡፡

**መልካም ዘመን በየዕለቱ በመልካም ሥራ የሚያሳልፉት ደቂቃና ሰዓት ድምር ውጤት ነው፡፡** ዘመን ሲለወጥ የዕድሜአችንን ቁጥር እየጨመረ የሚሔድ ሊመስለን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዷን ዕለት ውለን ስናድር የሰጠን ዕድሜ የዚያኑ ያህል እያለቀና ለሞትም እየቀረብን ነው፡፡ ስለዚህ አዲስ ዓመትም አዲስ ዕለትም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠን የምሕረት ዓመት /ዓመተ ምህረት/ ዕለተ ምህረት ነው፡፡ "ይህችን ዓመት ደግመ ተዋት" በሚለው የቅዱሳን ምልጃ ያገኘናት በመሆኗ አዲስ የሚሆነው የዘመኑ ቁጥር፣ ዕለትና ወር ብቻ ሊሆን አይገባም፡፡ ዕለት፣ ሳምንት፣ ወርና ዓመት ዑደታቸውን ጠብቀው የሚፈራረቁና አንዳቸው ወደ ሌላኛው የሚያደርሱን የጊዜ መሰላሎች ናቸው፡፡

**ዘመን መልካም የሚሆነውና አዲስ የሚያሰኘው የሥጋን ፈቃድ ስንከተል የኖርንባቸውን ዘመናት ትተን እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኝበትን ፈቃደ ነፍስን መከተልና መፈጸም ስንጀምር ነው፡፡ /1ኛ.ጴጥ.4÷3/፡፡** ስለዚህ በሶስተኛው ሺህ ዓመት ቁስቻችን ብቻ ሳይሆኑ ሥጋዊ ሐሳባችንና ተግባራችንም ለውጥ እንዲያገኝ ዘመኑን ዋጅተን እንድንዘጋጅ የእግዚአብሔር ቸርነት የወላዲተ አምላክ አማላጅነት አይለየን፡፡

መልካም ዘመን!!

***ምንጭ፡- ፍሬ ተዋሕዶ መጽሔት /2009 ዓ.ም./***